Amharic

# በቪክቶሪያ የምዝገባና የድምጽ አሰጣጥ ፈጣን መረጃ

## ቪክቶሪያ የምትስተዳደርበት ሁኔታ በዕለት ኑሮአችን ላይ ተጽእኖ አለው። ተመዝግቦ በመምረጥ ቪክቶሪያን መቅረጽ ይችላሉ።

## ለመምረጥ መመዝገብ

ለመምረጥ መመዝገብ ጠቀሜታ አለው። ምክንያቱም በፌደራል፣ በክልል ና በቀበሌ ደረጃዎች ባሉ መንግስታት የሚወክልዎትን መምረጥ ይችላሉ። እያንዳንዱ የመንግስት ደረጃ እርስዎንና ማሕበረ ሰብዎን ሊነካ የሚችል ኃላፊነት አለው።

በ ፌደራል፣ በክልልና በምክርቤት መረጣ በምርጫ መዝገብ በአግባቡ የተመዘገቡ መሆን አለብዎት።የምርጫ ምዝገባ ሚና የመራጮች ስምና አድራሻ መመዝገብ ነው።

### እንዴት ነው የምመዘገበው?

መመዝገብ ቀላል ነው። የሚያስፈልግዎት አንድ ጊዜ ብቻ በፌደራል፣ በክልል ና በምክር ቤት ምርጫ ተመዝግቦ መምረጥ ነው።

የሚያደርጉት ነገር ቢኖር ከVEC ዌብ ሳይት የመመዝገብያ ቅጽ ሞልተው መመለስ ብቻ ነው።

ቅጾች በፖስታ ቤቶች፣በኮልስና በ ባይሎ ሱፐር ማርኬት ወይም በ VEC ቢሮ ይገኛሉ። በ13 18 32 ብትደዉሉልን በ ፖስታ ቤት ልንልክላቹህ እንችላለን፣ አስተርጓሚ ካስፈለገም በ ስልክ ቁጥር 9209 0112 ደውሉልን።

### መመዝገብ አለብኝ?

አዎ፡

- የአውስትራሊያ ዜጋ ለሆነ
- ዕድሜው18ዓመትና በላይ ለሆነ
- አሁን ሚኖርበትበት አድራሻ ቢያንስ ለአንድ ወር በቪክቶሪያ ተቀማጭ ለሆነ ሁሉ መመዝገብ ግዴታ ነው።

### ልዩ ምዝገባዎች

ከታች ለተዘረዘሩ ለልዩ ሁኔታዎች አመዘጋገብ ከ VEC ዌብሳይት ወይም በ ስልክ ቁጥር 13 18 32 VEC ን በማነጋገር።ያገኛሉ አስተርጓሚ ሲያስፈልግ በ9209 0112 ይደውሉ።

#### ወደምርጫ ጣብያው መሄድ ካልቻልኩስ?

በምርጫው ቀን ወደ ምርጫው ጣቢያ በመሄድ ለመምረጥ የሚቸገሩ ከሆነ ፣አጠቃላይ በፖስታ መራጭ ሆነው እንዲመርጡ ማመልከት ይችላሉ።በፖስታ መራጭ መሆን የሚቻለው፣-

- ከምርጫ ጣቢያው 20 ኪሎሜትር ርቀው የሚኖሩ ከሆነ
- ህመምተኛ ከሆኑ ወይም ኣስታማሚ ከሆኑ
- ምርጫው ላይ እንዳይሳተፉ የሚከለክል ሃይማኖታዊ እምነት ላይ ከሆኑ
- ከ5 ዓመት በታችህ ተፈርዶብዎት እስርዎን በመፈጸም ላይ ከሆኑ
- በመጠርያ ቦታ የሚኖሩ ህመምተኛ ከሆኑ
- ስምዎ በመዝግብት እንዳይታዩ ሆነው ተመዝግበው ሳይለንት መራጭ ከሆኑ
- የ70 ዓመት ና ከዚያ በላይ ኣዛውንት ከሆኑ፦ለክልልና ለ ቀበሌ ምክርቤት ምርጫ ይፈቀዳል።

የፖስታ መራጭ ሆነው ተመዝግበው ከሆነ ዕጩ ተመራጮች ከታወቁ በኃላ ለመምረጥ የሚያስፈልጉ ነገሮች ይላክለዎታል።

ወደ ባህርማዶ የምሄድ ከሆንስ?

- ተመዝግበው ከሆነና በ3 ወር ጊዜ ውስጥ ከሀገር ውጭ የሚሄዱና በ6ወር ውስጥ ለመመለስ የሚያስቡ ከሆነ
- የተመዘገቡና ከ3 ዓመት ባነሰ ጊዜ ውስጥ ከኣውስትራሊያ የወጡ ና በ6 ዓመት ውስጥ ለሚመለሱ
- በባሕር ማዶ እየኖሩ ላሉና ላልተመዘገቡ፦

እንደ የባህር ማዶ መራጭ ሆነው መመዝገብ ይችላሉ።ይኸ ማለት ባሉበት ቦታ በኣካል ተገኝተው የኣውስትራሊያ ዲፕሎማት ኣገልግሎት በሚሰጥበት ቦታ ሄደው ወይም በፖስታ መራጭ ለመሆን በማመልከት ማለት ነው።

ለደህንነቴ ምክንያት ኣድራሻየ መመዝገብያው ውስጥ ባይሰፍርስ?
ስምዎ በመራጮች መዝገብ በመስፈሩ የርስዎና የቤተሰብዎ ደህንነትኣደጋ ላይ የሚጥል ሆኖ ካገኙት እንደ ሳይለንት ኢለክቶር ለመሆን ማመልከት ይችላሉ። ሳይለንት ኢለክተር ማለት ወደፊት በሚታተመው የመራጮች ዝርዝር ውስጥ ኣድራሻው የማይጻፍ ማለት ነው።

የምኖርበት ቤት የሌለኝና ቋሚ ኣድራሻ የሌለኝ ብሆንስ?
ቋሚ ኣድራሻ ከሌለዎት እንደ ኣድራሻ የሌለው መራጭ ሆነው እንዲመዘግቡ ማመልከት ይችላሉ።

## ልቀበሌ ምክርቤት ምርጫ መመዝገብ

ለመምረጥ ተምዝጊቤኣለሁ?

- ኣሁን ላሉበት ኣድራሻ በክልል መንግስትና በፌደራል የመራጮች መዝገብ ውስጥ ካሉ ወይም
- የማይኖሩበት ቢሆንም ምርጫ በሚካሄድበት ማዘገጃ ቤት ንብረት ካለዎት ለንብረቱ በተቀዳሚ ወይም በሁለተኛ ደረጃ በየጊዜው እንዲከፈል የተተመነ ገንዘብ የሚከፍሉበት ሪኮርድ ካለ
- ለዛው ምክርቤት የምክርቤት ምርጫ ለመሳተፍ ያመለከቱ ከሆነ በቀበሌ ምርጫ በቀጥታ መራጭ ነዎት።(ከታች ያለው ይመልከቱ)

ቢያንስ እድሜዎ18 ዓመት ከሞላዎት ለመመዝገብ ማመልከት ይችላሉ።

- ኣውስትራሊያዊ ካልሆኑና ነገር ግን ምርጫው በሚካሄድበት ማዘጋጃቤት ውስጥ ለመዘጋጃቤቱ በየጊዜው የተወሰነ ክፍያ የሚከፍሉ ከሆነ፣ ወይም

- ባሉበት ማዘጋጃቤት ለያዙት ይዞታ በታሪፍ የሚከፍሉ ከሆነና ምርጫው በሚካሄድበት ቦታ ሌላ የመራጭነት ኣግባብ ከሌለዎት ለምሳሌ የሱቅ ተከራይ ቢሆኑ ወይም ለክፍያ ተጠያቂ ሆነው በየጊዜው ማስታወሻ የሚጻፍልዎት ከሆነ ወይም ዋናው ባለ ቤት ወክለው እንዲመርጡ መተግመኛ ጽሁፍ የሰጥዎት ሲሆን
- ምርጫ በሚካሄድበት ማዘጋጃ ቤት ለማዘጋጃቤቱ የታሪፍ ክፍያ የሚከፍል ኩባንያ ዳሬክተር ወይም የድርጅት ጸሐፊ ከሆኑና በማዘጋጃ ቤቱ ሌላ ምንም የመራጭነት ኣግባብ ከሌለዎት

ከተዘረዘሩት ልዩ ሁኔታዎች ውስጥ የሚመለከትዎት ነገሮች ካሉ የቀበሌው ምክርቤትን ያነጋግሩ።

## የምዝገባ መረጃ ማግኘት የሚችል ማነው?

የምዝገባ መረጃን ለመጠበቅና የመራጩ ሚስጢር ለመጠበቅ VEC ፕራይቬሲ ፖሊሲ ኣውጥቷል።

*Electoral Act 2002* (Victoria) የሚጠይቀው ጉዳዩ ለሚመለከታቸው ዋና ኣካላት እንደነ የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ የፓርላማ ኣባሎችና ዕጩ ተመራጮች VEC ያለውን መረጃ እንዲያገኙ የሚያደርግ ነው።

*Electoral Act*( የምርጫ ሕጉ)VEC ግለሰቦችና ድርጅቶች መረጃ እንዲያገኙ ይፈቅዳል ይኽ ሊሆን የሚችለው የሕዝቡ የመረጃ ፍላጎትና የግለሰቦች የመረጃ ሚስጢር የሚጠበቅበት ሁኔታን ባገናዘበ መንገድ ነው።

የመራጮች ዝርዝር ያለበት መረጃ የተሰጣቸው የግለሰቦችና የድርጅቶች ስም ዝርዝር በ VEC ዌብ ሳይት ይገኛል። በግል የደህንነት ጉዳይ ዝርዝር ሁኔታቸው መዝገብ ውስጥ እንዳይታይ የሚፈልጉ መራጮች እንደ ሳይለንት ኢለክተር ሆነው እንዲመዘገቡ ማመልከት ኣለባቸው።

## በምርጫ ወቅት ድምጽ ኣሰጣጥ

ለመምረጥ ከተመዘገቡ በሁሉም የፌደራል፣የክልልና የቀበሌ ምክርቤት ምርጫ  መሳተፍ ግዴታ ነው። ያለበቂ ምክንያት ሳይመርጡ ከቀሩ የገንዘብ  ቅጣት ይጣልብዎታል። ቋሚ ኣድራሻ የሌላቸው መራጮችና 70ና ከ70 በላይ የሆኑ መራጮች የቀበሌ ምክርቤት ምርጫ ባይመርጡም ይቅርታ ይደረግላቸዋል።

**የፌደራል ምርጫ**

የፌደራል ምርጫ ሁልጊዜም የሚደረገው በቅዳሜ ቀን ሆኖ ራሱን የቻለ በኣውስትራሊያ ፌደራል የምርጫ ኮሚሽን (AEC)የሚካሄድ ነው። የፌደራል ምርጫ  ምርጫን እየተከተለ በየ3 ዓመቱ ይካሄዳል።
የኣውስትራሊያ ፌደራል ፓርላማ ሁለት ማለትም House of Representatives (የተወካዮች ምክር ቤት) ና Senate (ሕግ መወሰኛ ምክርቤትን) የያዘ ነው።

**ማንን እየመረጥኩ ነኝ?**
በፌደራል ምርጫ የሚመርጡት በ ሕዝብ ተወካዮችና በሕግ መወሰኛ የሚወክሉዎትን ነው።

አውስትራሊአ በ150 የተወካዮች ክፍል ትከፋፈላለች። ከነዚህ ውስጥ ቪክቶሪያ ለ 3 ዓመት የሚያገለግሉ 37 ተወካዮችን ትመርጣለች

በፌደራል ምርጫ ቪክቶሪያውያን መራጮች ለ6 ዓመት የሚያገለግሉ ከ አስራሁለቱ ስድስቱን ለሕግ መወሰኛ ይመርጣሉ።

## የክልል መንግስት ምርጫዎች

የክልል መንግስት መረጣ በየአራት ዓመቱ በኖቨምበር የመጨረሻ ቅዳሜ ቅዳሜ ራሱን ችሎ በ VEC የሚካሄድ ምርጫ ነው። በ 2006 እና በ2010 የክልል መንግስት ምርጫ ይኖራል።

የቪክቶሪያ ፓርላማ በ88 ሕግ አውጪ ጉባዔ ( Lower House)ወረዳዎች ናከ2006 የክልል መንግስት ምርጫ ወደ 8 የህግ አውጪ ምክርቤት( Upper House)ዞን የተከፈለ ነው።

### ማንን ነው የምመርጠው?

በ ክልል መንግስት መረጣ የሚመርጡት በሕግ መወሰኛ ጉባዔ የሚወክልዎት አንድ ሰው ና በ ሕግ አውጪ ምክርቤት የሚወክሉዎት 5 ተወካዮችን ነው።እነዚህ ተወካዮች ለ 4 ዓመት ያገለግላሉ።

## የቀበሌ ምርጫ

ለ 79የቪክቶሪያ ማዘጋጃ ቤቶች የቀበሌ ምክርቤቶች ምርጫ በየ4 ዓመቱ ኖቨምበር የመጨረሻ ቅዳሜ ይካሄዳል።

ምርጫው በፖስታ ወይም በአካል ቀርቦ ስም እየተቆጣጠሩ በቫሎት እንዲካሄድ ማድረግ የምክርቤታቹህ ምርጫ ነው።

### ማንን እየመርጥኩ ነኝ?

በቀበሌዎ ምክርቤት የሚመርጡት በቀበሌዎ ማዘጋጃቤት የምክርቤት አቫል የሚሆን ዕጩ ና ለ4ዓመት የሚያገለግል ማለት ነው። በ ሜልበርን ከተማም የከተማዋ ከንቲባና ምክትል ከንቲባ የሚሆኑ በቀጥታ ይመርጣሉ።

በቪክቶሪያ ያሉ የምርጫ ቀበሌዎች ስፋት ተመጣጣኝ አይደሉም ሰፊና ጠባብ ናቸው። ስለ ተመራጮች ብዛት ድልድልና ስለ የምርጫ አወቃቀር የሚወሰነው የአከባቢው ሚኒስቴር ነው።

## በበለጠ ለማወቅ እፈልጋለሁ?

**የአስተርጓሚ እርዳታ ከፈለጉና ስለ ፌደራል፣ክልልና ቀበሌ መንግስታት ምርጫ ምዝገባናና ድምጽ አሰጣጥ በበለጠ ለማውቅ ከፈለጉ በ** 9209 0190 **ይደውሉ።**

**ለአማራጭ በሚከተለው ያገኙናል**

Victorian Electoral Commission
Level 8, 505 Little Collins Street
Melbourne Victoria 3000

**ወይምበ** 13 18 32 **ይደውሉልን**
**ከአውስትራሊያ ውጭ ከሆነ በ** +61 3 9299 0520
**መስማት ለተሳናቸው የ ቴክስት ስልክ ቁጥር**9299 0570

**በፌደራል ምርጫ ለ ሕዝብ ተወካዮች ና ልሕግ መወሰኛ ተወዳዳሪ ዕጩ መጠቆም ከፈለጉ** AEC**ን በስልክ ቁጥር** 13 23 26 **ያነጋግሩ ወይም** www.aec.gov.au **ይመልከቱ**

**በቪክቶሪያ የክልል መንግስት የሕዝብ ተወካዮች ና የሕግ መወሰኛ ወይም የቀበሌ ምክርቤቶች ምርጫ ዕጩዎች ን** VEC.**ማነጋገር ኣለባቸው።**